የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 10
ADDIS ABABA - 24th August, 1995

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፯ ዓ.ም.
የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋሚያ
አዋጅ ..... ገጽ ፸፬

CONTENTS

Proclamation No. 10/1995
Disaster Prevention and Preparedness Commission Establishment Proclamation ..... Page 74.

አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፯

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

፩. "አደጋ" ማለት የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ወይም የአንድ አካባቢ ነዋሪ በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የምግብና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ሳይችል ቀርቶ በዘወትር አኗኗሩ ላይ ቀውስ በመድረሱ ያለ ሌሎች እርዳታ ኑሮውን ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ መከሰት ነው ፣

፪. "ዕርዳታ" ማለት የአደጋ ሰለባዎችን የምግብና ሌሎች መሠረታዊ የኑሮ ፍላጎቶቻቸውን ከማሟላት በተጨማሪ አደጋ የደረሰበት አካባቢ ለወደፊቱ ለተመሣሣይ አደጋ እንዳይጋለጥ የሚወሰዱ ሁለገብ እርምጃዎችን ያጠቃልላል ፣

PROCLAMATION NO. 10/1995
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE DISASTER PREVENTION AND PREPAREDNESS COMMISSION

WHEREAS, it is found necessary to establish the Disaster Prevention and Preparedness Commission;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Disaster Prevention and Preparedness Commission Establishment Proclamation No. 10/1995."

2. Definitions

In this Proclamation:

1) "Disaster" means the development of a situation wherein a segment of the community or the population of a locality cannot any longer meet the need for food and other basic necessities, due to natural or man-made calamities, with its daily life thus falling into crisis which renders it unable to survive without assistance from others;

2) "Assistance" includes comprehensive measures taken to prevent the coming, in future, of a disaster area under a similar situation, in addition to meeting the need of the victims of disaster for food and other basic necessities of life;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1-60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ቮ· "የዕርዳታ ፕሮግራም" ማለት የምግብና ሌሎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች አቅርቦትና ሥርጭት ፣ ንፁህ የመጠጥ ውኃ መኖርን ፣ የጤናና የተመጣጠነ ምግብ ድጋፍን ፣ ለአረጋውያንና ለአካለ ስንኩላን የሚሰጡ ድጋፎችን ፣ እንደ እንስሳት የመሳሰሉ የገጠሩን ጥሪት ከእልቂት ማዳንን ፣ ከእርሻው ውጭ ተዳባይ የሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲጐለብቱ መርዳትን ፣ አካባቢን መልሶ መገንባትን ፣ ድርቅን ለመቋቋም የሚያስችሉ ሌሎች የልማት ተግባሮችን እና ከዕርዳታ ጋር በተያያዘ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ዕቅዶችን የሚመለከቱ እርምጃዎችን ያጠቃልላል ።

ቯ· መቋቋም

፩· የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፪· ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል ።

፭· ዓላማ

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፤

፩· ኅብረተሰቡን ለአደጋ የሚያጋልጡ መሠረታዊ መንስኤ ዎችን በማስወገድ አደጋን መከላከል ፤

፪· አደጋ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አቅምን አስቀድሞ ማጎልበት ፤

፫· ለአደጋ ሰለባዎች አስፈላጊው ዕርዳታ በወቅቱ መድረሱን ማረጋገጥ ።

፮· ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ፖሊሲ ያዘጋጃል ፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ፤

፪· ለአደጋ የተጋለጡ አካባቢዎችን በማጥናት ለወደፊቱ አደጋን ለመከላከል የሚረዱ ስልቶችን ይቀይሳል ፤

፫· ብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድንና ብሔራዊ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትን ያስተዳድራል ፤

፬· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ መንስ ኤዎችን አስቀድሞ ያጠናል ፤ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትም ይዘረጋል ፤

፭· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ በሚደር ስበት ጊዜ የጉዳቱን መጠንና ስፋቱን ፣ መወሰድ ከሚገባው እርምጃ ጋር ያሳውቃል ፣ አደጋው የሚመለ ከተው ሥፍራም አደጋ የደረሰበት ሥፍራ መሆኑን በይፋ ይገልጻል ፤

፮· ከመንግሥት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ማናቸውንም ዓይነት ዕርዳታ ይጠይቃል ፣ ይቀበላል፤

፯· በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚሰጠውን ማናቸ ውንም ዓይነት ዕርዳታ ይመዘግባል ፣ ለተረጂዎች እንዲ ደርስ ያደርጋል።

፰· ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ስለተገኘው ዕርዳታ ዓይነት ፣ መጠንና አጠቃቀም በመገናኛ ብዙሀን ለሕዝብ ያሳውቃል ፤

3) "Assistance Programme" includes the supply and distribution of food and other materials necessary for a living, the availability of clean rinking-water, support in health and nutrients, support extended to the elderly and the disabled, the prevention of destruction to rural wealth such as animals, support for the development of supplementary economic activities besides agriculture, the rehabilitation of the environment, other developmental activities that help combat drought and measures relating to schemes which create job opportunities in connection with assistance.

3. Establishment

1) The disaster Prevention and Preparedness Commission /hereinafter referred to as the "Commission"/ is hereby established as an autonomous public institution of the Federal Government.

2) The Commission shall be accountable to the Council of Ministers.

4. Head Office

The head office of the Commission shall be in Addis Ababa.

5. Objective

The Commission shall have the following objectives:

1) to prevent disasters by way of removing the basic causes thereof;
2) to build, in advance, the capacity necessary to alleviate the extent of damages that could be caused by disasters;
3) to ensure the timely arrival of necessary assistance to victims of disaster.

6. Powers and Duties of the Commission

The commission shall have the following powers and duties:

1) to prepare a disaster prevention and preparedness national policy; formulate strategy for its application; and, upon approval, follow up its implementation;
2) to formulate strategies for future disaster prevention by way of studying previous disaster areas;
3) to administer the National disaster Prevention and Preparedness Fund and the National Food Reserve;
4) in cooperation with the concerned organs, to undertake prior studies on the causes of disaster; set up systems for advance warning;
5) in cooperation with the concerned organs, to make known the magnitude and extent of a disaster together with measures that should be taken in connection therewith; officially declare any relevant part of the country a disaster area;
6) in accordance with directives issued to it by the government, request for and receive any form of assistance from domestic and foreign sources;
7) to register all forms of assistance received from domestic and foreign sources and cause the distribution of same to the people being helped;
8) to inform the public through the mass media of the type, volume and utilization of assistance received from domestic and foreign sources;

፱· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ሰለባ ዎችን መልሶ ያቋቁማል ፤

፲· መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን የዕርዳታ ተግባር ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ፤

፲፩· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ ውል ይዋዋላል ፣ በስሙ ይከሳል ፣ ይከሰሳል ፤

፲፪· ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፯· <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ ፤

፩· የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) ፣

፪· በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነርና አንድ ምክትል ኮሚሽነር ፣ እና

፫· አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፰· <u>የኮሚቴው አባላት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፤

፩· በመንግሥት የሚሰየም ኃላፊ	.....	ሰብሳቢ
፪· የግብርና ሚኒስትር	.....	"
፫· በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የክልል ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ	.....	አባል
፬· የገንዘብ ሚኒስትር	.....	"
፭· የጤና ጥበቃ ሚኒስትር	.....	"
፮· የመከላከያ ሚኒስትር	.....	"
፯· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር	.....	"
፰· የሥራና የከተማ ልማት ሚኒስትር	.....	"
፱· የኮሚሽኑ ኮሚሽነር	.....	"

፱· <u>የኮሚቴው ስብሰባ</u>

፩· ኮሚቴው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል ።

፪· ከኮሚቴው አባላት አብዛኞቹ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል ።

፫· የኮሚቴው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ።

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፲· <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ፖሊሲ ላይ ይመክራል ፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል ፤

፪· አደጋ የደረሰበት ሥፍራ በይፋ እንዲገለጽ ይወስናል ፤

፫· የዕርዳታ ፕሮግራሞችን በመገምገም አስፈላጊውን የዕርዳታ ወጭ እንዲመደብ ያደርጋል ።

፬· የዕርዳታ ፕሮግራሞች የአደጋ መሠረታዊ መንስኤዎችን በማስወገድና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋል ።

፭· በልማት መስኮች የአደጋ መከላከል ፕሮግራሞች ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው ያደርጋል ።

9) in cooperation with the appropriate organs, to rehabilitate victims of disaster;

10) to coordinate and supervise relief activities of non-governmental aid organizations;

11) to own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

12) to carry out such other activities as would enhance the attainment of its objectives.

7. Organization of the Commission

The commission shall have.

1) a Disaster Prevention and Preparedness National Committee (hereinafter the "Committee");
2) a Commissioner and Deputy commissioner appointed by the Government; and
3) the necessary staff.

8. Members of the Committee

The Committee shall have the following members:

1) an Official to be designated by the Government	.....	Chairman
2) the Minister of Agriculture	.....	"
3) the Head of the Regional Affairs Sector in the Office of the Prime Minister	.....	Member
4) the Minister of Finance	.....	"
5) the Minister of Health	.....	"
6) the Minister of Defence	.....	"
7) the Minister of Economic Development and Cooperation	.....	"
8) the Minister of Public Works and Urban Development	.....	"
9) the Commissioner of the Commission		"

9. Meetings of the Committee

1) The committee shall hold a regular meeting twice annually; however, it may at any time hold an extraordinary meeting, whenever found necessary.
2) There shall be a quorum where the majority of the members of the Committee are present at its meetings.
3) Decisions of the Committee shall be passed by a majority vote; in case of a tie the Chairman shall have a casting vote.
4) Without prejudice to the other provisions of this Article, the Committee may draw up its own rules of procedure.

10. Powers and Duties of the Committee

The committee shall have the following powers and duties:

1) to deliberate upon the national policy for disaster prevention and preparedness; ensure its implementation on being approved;
2) to decide on the official declaration of a disaster area;
3) to cause the allocation of expenditure for assistance to be made subject to evaluation of assistance programmes;
4) to make assistance programmes have their emphasis on removal of the basic causes of disaster and on lending input to a continuous economic development;
5) to see to it that disaster prevention programmes receive due attention in development activities.

፲፩· የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

፩· ኮሚሽኑ የኮሚሽኑ ዋና አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል ፣

ለ) የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ያስተዳድራል ፣

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ፣

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፣

ሠ) ኮሚሽኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙ ነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል ፣

ረ) ስለ ኮሚሽኑ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል ።

፫· ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ከተግባሩ በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊ ዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል ።

፲፪· በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል ።

፲፫· የሂሳብ መዛግብት

፩· ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል ።

፪· የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው አዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ ።

፲፬· የተሻረ ሕግ

የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር ፭፻፫፫/፲፱፻፫፪ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፲፭· መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ

9በአዋጅ ቁጥር ፭፻፫፫/፲፱፻፫፪ ተቋቁሞ የነበረው የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል ።

፲፮· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

11. Powers and Duties of the Commissioner

1) The commissioner shall be the chief executive of the Commission and, as such, shall direct and administer the activities of the commission.

2) Without limiting the generality stated in sub-Article (1) of this Article, the Commissioner shall:

(a) exercise the powers and duties of the Commission specified in Article 6 of this Proclamation;

(b) employ and administer employees of the commission in accordance with the Federal civil service laws;

(c) prepare the annual work programme and budget of the Commission and implement same upon approval;

(d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Commission;

(e) represent the Commission in all its dealings with third parties;

(f) submit reports on the activities of the Commission.

3) The commissioner may delegate part of his powers and duties to the other officials and employees of the Commission to the extent necessary for the efficiency of the Commission.

12. Budget

The budget of the Commission shall be allocated by the Government.

13. Books of Accounts

1) The commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2) The commission's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor general or by auditors designated by him.

14. Repeal

The Relief and Rehabilitation Commission Establishment Proclamation No. 173/1979 (as amended) is hereby repealed.

15. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Relief and Rehabilitation Commission, previously established under Proclamation No. 173/1979, are hereby transferred to the Commission.

16. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of August, 1995.

Done at Addis Ababa, this 24th day of August, 1995.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE